# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** JEA-RB፣ JED፣ JED-RE፣ JEE-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** Chief of Teaching, Learning, and Schools

## አለም አቀፍ የውጭ አገር ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ

I. **ዓላማ**

ስለ ውጭ አገር ተማሪዎች እና አለምአቀፍ ተማሪዎች ምዝገባ እና የምደባ ሂደትበሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MCPS ፖሊሲ JEA መሠረት ነዋሪነት፣የትምህርት ክፍያ፣እና የምዝገባ ሒደት መመሪያ፣እና MCPS ደንብJEA-RB፣የተማሪዎች ምዝገባ፣እና MCPS ደንብ JEA-RE፣በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሰረተ የተማሪዎች የምዝገባ ሥርአት መደንገግ።

II. **ትርጉም**

A. ዓለም አቀፍ ተማሪዎች እንደሚከተለው ይገለጻሉ –

1. ከዩናይትድ ስቴትስ እና ከግዛቷ ውጭ ከሆኑ ሀገሮች ለትምህርት የሚመጡ ተማሪዎችን እና (ለምሳሌ፡- በመከላከያ ዲፓርትመንት የሚካሄድ ት/ቤት ወይም እውቅና ያለው በውጭ ሀገር የሚገኝ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ት/ቤት ውስጥ ያልተማሩ) እንዲሁም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ በዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤት ተመዝግበው ያልተማሩ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎች።

2. ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ በሆነ ሀገር ትምህርት ቤት ገብተው ከሁለት ዓመት በላይ የተማሩ የአሜሪካ ዜጎች። ይህ በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሚተዳደሩ የዩ.ኤስ መከላከያ ዲፓርትመንት ትምህርት ቤቶችን፣ ወይም እውቅና ያላቸው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤትቶች ውስጥ የተማሩ ተማሪዎችን አያካትትም።

B. የውጭ ሀገር ተማሪ ማለት በተማሪ ቪዛ ለትምህርት ወደ ዩናይትድ ስቴት የመጣ(ች) ማንኛውም እድሜው(ዋ) ለትምህርት የደረሰ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

1. ኤክስቼንጅ ተማሪ ማለት፡- J-1 ቪዛ (J-1) ያለው/ያላት እና ፈቃድ ባለው የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ውስጥ የታቀፈ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

2. ስደተኛ ያልሆነ(ች) ተማሪ ማለት፡- በዩ.ኤስ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት (INS) የፀደቀ F-1 ቪዛ (F-1) ያለው/ያላት ተማሪ ማለት ነው።

III. **ዳራ**

A. አለም አቀፍ የተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ ቢሮ (IAE) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ስደተኛ ያልሆኑ ጎብኝዎችን (F-1) እና የኤክስቼንጅ ተማሪዎችን (J-1) የመመዝገብ ሂደቶች እና ደንቦች መከበራቸውን ለመከታተል እና ለማስፈፀም ስልጣን ያለው ብቸኛው አካል ነው።

B. የሚከተሉት ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከመመዝገባቸው በፊት ወደ IAE መሄድ አለባቸው፡-

1. አለም አቀፍ ተማሪዎች

2. በ ዩ.ኤስ ትምህርት ቤት፣ እውቅና በተሰጠው አሜሪካን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት፣ ወይም በ ዩ.ኤስ መንግስት የሚካሄድ ት/ቤት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በማንኛው ጊዜ ያልተከታተሉ የዩ.ኤስ ዜጎች።

3. ከውጭ የመጡ ተማሪዎች፣ ስደተኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን (F-1) እና በተማሪዎች ኤክስቼንጅ የሚመጡ ተማሪዎችን (J-1) ጨምሮ

C. ባለፉት ሁለት ዓመታት በዩ.ኤስ የትምህርት ሲስተም የተከታተለ(ች) ተማሪ በአካባቢ ት/ቤት (ሆም ስኩል) ወይም ኮንሰርሽያ ጽ/ቤት (consortia office) መግባት ይችላል/ትችላለች።

D. IAE የትምህርት ማስረጃዎችን/የትምህርት ሰነዶችን በማስተርጎም ይረዳል።

E. IAE በሜትሮፖሊታን የውጭ ሀገር ተማሪዎች አማካሪዎች ማህበር (MAFSA) ብሄራዊ የውጤት አሰጣጥ ሚዛንን መሰረት በማድረግ የክፍል ምደባ እና የክሬዲት አሰጣጥ ትራንስክሪፕቶችን ይገመግማል።

## IV. የአፈጻፀም ሒደት

A. የወላጅ/የሞግዚት/የስፖንሰር ኃላፊነቶች

1. የት/ቤት መግቢያ ቀጠሮ ለማግኘት የተማሪ(ዎች) መገኘት አስፈላጊ ስለሆነ ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ምዝገባና ምደባ ጽ/ቤት (IAE) ያነጋግሩ።

2. MCPS ቅጽ 560-24፣የአዲስ ተማሪ መረጃ ይሙሉ።

3. JEA-RB ደንብየተማሪዎች ምዝገባና ምደባቅጽ ላይ በተዘረዘረው መሠረት፣የመመዝገቢያ ሰነዶች ወደ IAE መቅረብ አለባቸው።

4. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ከፊል እና ወቅታዊ የትምህርት ዓመት ሪኮርድ እና ብሔራዊ የፈተና ውጤቶችን ጭምር የመጨረሻውን ኦፊሴላዊ የትምህርት ማስረጃዎች (እንደ አስፈላጊነቱ ከኦፊሴላዊ ትርጉም ጋር) ያቅርቡ።

a) በኤለመንተሪ እና ሚድል ስኩል እድሜ ለሚገኙ ተማሪዎች፥ ተማሪው/ዋ/ዎቹ ባለፈው ዓመት ትምህርት ቤት የተከታተለ(ች)በት/የተከታተሉበት ህጋዊ የትምህርት ቤት ሪከርዶች ያስፈልጋሉ።

b) የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ተማሪው(ዋ) ባለፉት ሦስት ዓመታት ትምህርት ቤት የተከታተለ(ች)በት ህጋዊ ሪኮርዶች ያስፈልጋሉ።

c) ቅጂ የትምህርት ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸውም፣ ነገር ግን ትምህርት ቤቶች ሪኮርዶችን በኢሜል፣ፒ.ዲ.ኤፍ አባሪ በማድረግ ወይም በመደበኛ ፖስታ በቀጥታ ወደ

IAE መላክ ይችላሉ።

d) ለመመረቅ የደረሱ፣ ነገር ግን የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በሚመለከት፥ተማሪው(ዋ)ን አለመመረቅ የሚያረጋግጥ ከትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ተማሪው(ዋ) ለመጨረሻ ጊዜ በተማረ(ች)በት ዲስትሪክት ካለው ተመጣጣኝ ስልጣን ካለው አካል የተጻፈ ማረጋገጫ ማቅረብ ያስፈልጋል።

e) ከዩ.ኤስ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ያጠናቀቁ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የመመዝገቢያ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ትራንስክሪፕታቸው (በካምብሪጅ የምዘና እና አለምአቀፍ ትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትራንስክሪፕት ግምገማ ወይም ብሔራዊ ፈተና) ተጨማሪ ግምገማ ሊደረግ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

B. IAE ሃላፊነት፦

1. አለም አቀፍ ተማሪዎችን የመመዝገብና ት/ቤት የመመደብ ሒደት፦

a) የእያንዳንዱን ተማሪ የልደት ቀን እና የክትባት ማስረጃዎችን፣ የወላጅ/የአሳዳጊ ማንነትን እና የነዋሪነት ቦታ ማረጋገጥ እና አስፈላጊ ከሆነ የተማሪው(ዋ)ን የቪዛ ሁኔታ ማጣራት።

b) የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት ታሪክ መገምገም፣ የትምህርት ማስረጃዎችን መገምገም፣ የመጨረሻ/ኦፊሴላዊ የትምህርት ቤት ሪኮርዶችን መገምገም፣ በሜሪላንድ ስቴት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች መሰረት ይፋዊ የትምህርት ቤት ክሬዲቶችን መገምገም፤ የትምህርት ቤት ምደባን መወሰን፣ እና የክፍል ደረጃ ምደባን ማማከር።

c) ተማሪው(ዋ) ወደ MCPS ለመግባት የሚያስችልና ከ ዩ.ኤስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ጋር የሚመጣጠን ትምህርት በሌላ የትምህርት ሥርአት ማጠናቀቁ(ቋ)ን በመገምገም ይወስናል።

d) በግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም ወይም ተመጣጣኝ ስነልቦናዊ ወይም የትምህርት ምዘናን ጭምር ለልዩ ትምህርት/ስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎት የእያንዳንዱን ተማሪ ሪከርድ ሠነዶችን/ዶክመንቶችን መገምገም።

እንደዚህ አይነት ሰነዶች ካሉ IAE ሱፐርቫይዘር ተማሪው(ዋ) ለመመዝገብ ብቁ ለሚሆንበት ትምህርት ቤት ርእሰመምህር እና እንዲሁም በዚያ ትምህርት ቤት ለተመደበ(ች)ው የልዩ ትምህርት ክላስተር ሱፐርቫይዘር ያሳውቃል።

e) የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልግ ለማጣራት በምዝገባው ሂደት ያለውን መረጃ በመለየት የትምህርት ቤቱ ቡድን ተማሪው(ዋ)ን እንዲከታተል ሊመራ ይችላል።

IAE ሱፐርቫይዘር ይህንን መረጃ ተማሪው ለመመዝገብ ብቁ ለሆነበት ለት/ቤት ርእሰመምህር እና እንዲሁም በዚያ ትምህርት ቤት ለተመደበ የልዩ ትምህርት ክላስተር ሱፐርቫይዘር ሪፖርት ያደርጋል።

f) ESOL ተማሪዎች ቀደም ሲል በተለያየ ዘርፍ የወሰዱት የስልጠና ትምህርት ፕሮግራም

(Multidisciplinary Education Training and Support (METS) Program) በጣም ውስን ወይም ምንም ያልወሰደ(ች) መሆኑን መለየት።

g) IAE የምዝገባ እና የምደባ ሒደት ማጠናቀቅ

h) አስፈላጊ ከሆነ ስለ መኖሪያ እና የትምህርት ክፍያን በሚመለከት መውሰድ ያለባቸውን ቀጣይ እርምጃዎች ለወላጅ/ለአሳዳጊ ያሳውቃል።

2. ኤክስቼንጅ ተማሪዎችን የመቀበል ሒደት

a) MCPS በኤክስቼንጅ ፕሮግራም ወደ አሜሪካ ለሚገቡ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ የሆነ ተቀባይ ቤተሰብ ጋር የሚቆዩ ከሆነ ቢበዛ ለሁለት አካዳሚክ ሴሚስተር ነፃ ትምህርት ይሰጣል።

b) ከተጠየቀ፣MCPS ለኤክስቼንጅ ተማሪዎች፣ ለወላጆቻቸው/ለአሳዳጊዎች፣ ለአስተናጋጅ ቤተሰቦች ወይም ለተማሪ ኤክስቼንጅ ድርጅት የተማሩበትን ሪፖርት ካርድ የመሳሰሉ መደበኛ ያልሆኑ ሪኮርዶችን መስጠት ይችላል።

c) በአንድ የትምህርት ዓመት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኤክስቼንጅ ተማሪዎች ቁጥር ቢበዛ ከ 50 መብለጥ የለበትም እና በአንድ የ MCPS ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ 5 ተማሪዎች መብለጥ የለበትም።

d) IAE ሱፐርቫይዘር የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ የአመልካቹ(ቿ)ን ብቁነት በማረጋገጥ ይወስናል/ትወስናለች።

(1) የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅቱ አለም አቀፋዊ የትምህርት ጉዞ ደረጃ የሚያሟላ ስለመሆኑ በካውንስል መፅደቅ አለበት።

(2) የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅቱ በዩናይትድ ስቴትስ የስቴት ዲፓርትመንት "United States Department of State፡ የተሰጡትን የፌደራል ድንጋጌዎች ማክበር አለበት።

(3) የኤክስቼንጅ ተማሪን ለመመዝገብ እና ለመቀበል የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅቱ አግባብነት ያላቸውን MCPS ደምቦች እና መመሪያዎችን ማክበር ይኖርበታል።

(4) ኃላፊነት ያለው የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅት ተወካይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ 120 ማይል ጅኦግራፊያዊ ክልል የሚኖር/የምትኖር መሆን አለበት። ይህ ሰው MCPS ውስጥ ስለተመደበ(ች)ው ተማሪ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

(5) አመልካቹ(ቿ) ወደ MCPS ከመግባቱ(ቷ) በፊት በሚኖርበት/በምትኖርበት አገር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የትከታተለ(ች) እና እድሜው(ዋ) ቢያንስ 15 ዓመት እና ከ 17 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበ(ባ)ት።

(6) አመልካቹ(ቿ) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር የሚመጣጠን ፕሮግራም ያጠናቀቀ(ች) መሆን የለበ(ባ)ትም። የኤክስቼንጅ ተማሪዎች ለዲፕሎማ፣ ለምረቃ፣ ወይም ለክሬዲት ግምገማ ብቁ አይሆኑም።

(7) የኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅት አመልካቹ(ቿ) ትምህርት ለሚከታተልበት/ለምትከታተልበት ወቅት የሚያገለግል ወቅታዊ J-1 ቪዛ እንዲኖረው/እንዲኖራት እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህጋዊ/በቋሚነት ነዋሪ ከሆነ ተቀባይ ቤተሰብ ጋር እንደሚኖር/እንደምትኖር ማመቻቸት አለበት።

(a) ማመልከቻው ከመፈቀዱ በፊት ተቀባይ ቤተሰቦች በተሳካ ሁኔታ የወንጀል ታሪክ ማጣራት አለባቸው።

(b) በጊዜያዊነት ከሚቀበሉ ቤተሰቦች ጋር የሚኖሩ አመልካች ተማሪዎችን ማመልከቻ MCPS አያጸድቅም። ከተቀባይ ቤተሰብ ጋር አስቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረ፣የውጭ ተማሪ ኤክስቼንጅ ፕሮግራም ድርጅት ተማሪው(ዋ) በተመዘገበ(ች)በት ተመሳሳይ የትምህርት ቤት ክላስተር ውስጥ መቀጠል እንዲችል/እንድትችል የሚረዳ ሌላ ተቀባይ ቤተሰብ የማግኘት ሃላፊነት አለበት። ተማሪው(ዋ) ተቀባዩ ቤተሰብ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ወደሚያገለግል ትምህርት ቤት ይላካል/ትላካለች።

(8) የመቀበያው ጊዜ ከአንድ እስከ ሁለት ሴሚስተር ሙሉ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከ MCPS አካደሚያዊ ካለንዳር በተቃራኒ ከሚጠቀሙ አገሮች የሚመጡ ተማሪዎች በሁለት ተከታታይ አካዳሚያዊ የካላንደር ዓመት ሁለቱን ሴሚስተሮች ለመማር ይችላሉ።

(9) የአመልካቹ(ቿ) ወቅታዊ የቪዛ እና የተወሰዱ ክትባቶች ሁኔታ መጣራት አለበት።

(10) የአመልካቹ(ቿ) የትምህርት ውጤት B ወይም ተመጣጣኝ የሆነ፣ ወይም ከዚያ የተሻለ አማካይ ውጤት መሆን አለበት።

(11) አመልካቹ(ቿ) መልካም ስነምግባር እንዳለው/እንዳላት እና የተለየ የትምህርት ቤት አካባቢ ጋር የመላመድ ችሎታ እንዳለው/እንዳላት የሚያረጋግጥ የትምህርት ቤት ድጋፍ (ሪኮመንዴሽን) ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

(12) አመልካቹ(ቿ) ESOL ድጋፍ ሳይኖር ትምህርቱ(ቷ)ን በእንግሊዝኛ ለመማር እንደሚችል/እንደምትችል ምዘና በመውሰድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት እንዳለው/እንዳላት መረጋገጥ አለበት።

e) ለቀጣይ የትምህርት ዓመት የኤክስቼንጅ ተማሪዎችን ማመልከቻዎች እና ደጋፊ ሠነዶችን መቀበል የሚቻለው ከኤፕሪል 15 እስከ ጁን 30 ብቻ ሲሆን፥ በወቅቱ የትምህርት ዓመት ለሁለተኛ ሰሚስተር ማመልከቻ እና ደጋፊ ሠነዶችን መቀበያ ጊዜ ከኦክቶበር 15 እስከ ዲሰምበር 15 ይሆናል። (MCPS ቅጽ 335-66 ይመልከቱMCPS የኤክስቼንጅ ተማሪ መቀበያ ማመልከቻ)

f) IAE የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኤክስቼንጅ ተማሪዎች ምዝገባ እና አቀባበል መመሪያ MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል።

3. I-20፣ስደተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት-I የተማሪን ሁኔታ የሚጣራበት (ቅጽ I-20) የውጭ አገር አመልካች ተማሪዎችን የማጣራት ሂደት።

a) በሌላ ሀገር የሚኖሩ እና ለትምህርት ብቻ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚመጡ የውጭ ሀገር ተማሪዎች MCPS ነዋሪ ተማሪዎች ስላልሆኑ IAE ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡበትን I-20 ቅጽ ይሞላል።

b) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) I-20 ቅጽ ለመሙላት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው:-

(1) የአመልካቹ(ቿ) ወላጆች በዩናይትድ ስቴትስ ነዋሪ አለመሆናቸው።

IAE የአመልካች ተማሪ የክትባት ማስረጃዎችን፣ የቪዛ ሁኔታ፣ እና የአመልካቹ(ቿ) ስፖንሰር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ መሆኑን ያረጋግጣል።

(2) የአመልካቹ(ቿ) እድሜ ቢያንስ 15 አመት እና 17 አመት ያልበለጠ፣ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ተመጣጣኝ ትምህርት ያጠናቀቀ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት።

(3) MCPS ደንብ JEE-RA ስለ ተማሪዎች ዝውውር ባለው ድንጋጌ መሠረት፥ ተቀባዩ ትምህርት ቤት ቦታ ካለው እና የተጨናነቀ አለመሆኑን መረጋገጥ ይኖርበታል።

(4) የአመልካቹ(ቿ) የእንግሊዘኛ ብቃት ምዘና ያለ ESOL ድጋፍ በእንግሊዝኛ የመማር ችሎታ እንዳለው/እንዳላት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

(5) የአመልካች የትምህርት ቤት ሪከርዶች B ወይም የተሻለ አማካይ ውጤት፣ ወይም ተመጣጣኝ ውጤት መሆኑ ማረጋገጥ።

(6) ስለ ተማሪው(ዋ) መልካም ስነምግባር እና የተለየ የትምርት አካባቢን የመልመድ ችሎታ እንዳለው-እንዳላት አመልካቹ(ቿ) የትምህርት ቤት ድጋፍ ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

(7) I-20 ቅጽ ላይ እንደተመለከተው የአመልካቹ ስፖንሰር ለታቀደው የቆይታ ጊዜ የትምህርት ቤቱን ክፍያ በቅድሚያ ይከፍላል።

(8) የአመልካች ስፖንሰር ተማሪው(ዋ)ን በሚያስፈልገው-በሚያስፈልጋት ነገር ለመደገፍ የፋይናንስ አቅም እንዳለው/እንዳላት የሚያረጋግጥ ማስረጃ መስጠት አለበ(ባ)ት።

(9) የአመልካች ስፖንሰር ከአመልካች ወላጆች የተጻፈ የሰነድ ማረጋገጫ ማህተም ያለው ደብዳቤ ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

c) የመግቢያ ጊዜ ከአንድ ሙሉ ሴሚስተር እስከ ቢበዛ አንድ የትምህርት ዓመት ሊሆን ይችላል።

d) ለቀጣዩ/መጪው የትምህርት ዓመት የ " I-20 Forms" ማመልከቻዎች ተቀባይነት

የሚኖራቸው ከኤፕሪል 15 እስከ ጁን 30 ሲሆን፥ እየተካሄደ ላለው የወቅቱ የትምህርት ዓመት ለሁለተኛ ሰሚስተር ማመልከት የሚቻለው ከኦክቶበር 15 እስከ ዲሰምበር 15 ነው።

e) I-20 ቅጽ መሙላት ያለባቸውን ተማሪዎች IAE የዩናይትድ ስቴትስ የሀገር ውስጥ ደህንነት መምሪያ (DHS) ስደተኛ ያልሆነ(ች) ተማሪን ሁኔታ በሚመለከት መመሪያዎችን በማክበር የመርዳት ሃላፊነት አለበት።

C. የአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ ኃላፊነቶች

1. ቀጥተኛ ጥያቄዎች እና ከህዝባዊ እና ከግል ድርጅቶች እና በግለሰቦች በኤክስቼንጅ ተማሪነት የመጡ የውጭ አገር ተማሪዎች የምዝገባና የምደባ ሒደት፣(J-1)እና ስደተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች(F-1) እና ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ በአሜሪካን ትምህርት ቤት ያልተከታተሉ አሜሪካዊያን ዜጎችን ጭምር ሁሉንም ሰነዶች ለ IAE ለግምገማ መቅረብ አለበት።

2. በማንኛውም የስደት ጥያቄ ቅጽ ላይ አትፈርም(ሚ)። ከ DHS እነዚያን ቅጾች እንዲፈርም MCPS ውስጥ የተፈቀደለት ብቸኛው አካል IAE ነው።

3. IAE ካጠናቀቀ በኋላ አለምአቀፍ ኤክስቼንጅ ተማሪዎችን እና ስደተኛ ተማሪዎችን መመዝገብ ይቻላል። IAE የምዝገባ ቅጽ "ተማሪው(ዋ) ከመመዝገቡ(ቧ) በፊት የትምህርት ክፍያ መከፈል አለበት፤ ወይም የትምህርት ክፍያ መከፈል እንደሌለበት IAE ማጽደቅ አለበት" የሚል ማህተም ከተደረገ፥ የትምህርት ክፍያ መፈፀሙን ወይም ከ IAE ክፍያ የተሠረዘለ(ላ)ት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከተቆጣጣሪው ክፍል እስኪደርስ ተማሪው(ዋ) መመዝገብ የለበ(ባ)ትም።

4. የጸደቀው የአካዳሚክ መርሃ ግብራቸው ሲጠናቀቅ የኤክስቼንጅ ተማሪዎች እና ስደተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ይለቃሉ።

D. የምዝገባ ይግባኝ የሚቀርብበት ሂደት

ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ MCPS ደንብ KLA-RA አሳሳቢ ስጋት፣ ቅሬታ ይግባኝ በሚለው ላይ በተገለጸው መሰረት፣15 ቀናት ውስጥ የ IAE ዲሬክተሩን ውሳኔ በቀጥታ ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ሰክሽን IV.D. ይመልከቱ።

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-**የሜሪላንድ ህግ ኮድ §13A.03.02.09

**የደንቡ ታሪክ፡-** ቀደም ሲል ደንብ 560 -1 እና JED-RA አካል ሲሆን ኦገስት 26 ቀን 1987 እንደ አዲስ የተለየ ደንብ ተመሠረተ። ሜይ 2 ቀን 1995 ተሻሽሏል፣ጁላይ 6 ቀን 2001 ዓ.ም እንደገና ተሻሽሏል። ሴፕተምበር 15 ቀን 2003 ዓ.ም ተሻሽሏል፤ ፌብሩዋሪ 24፣ 2005 ተሻሽሏል፣ ኖቨምበር 21 ቀን 2006 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 19 ቀን 2011 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ ማርች 5፣ 2021ተሻሽሏል፣ ጁን 5፣2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
| --- | --- |
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጎጎብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024